

# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

## የዕለት እንጀራ የዐቢይ ጾም (፰ኛ)

[፫፻፸ኛው እንጀራ] ሳምንቱ - ቅድስት የካቲት ፱ ፳፻፱



ወደ እግዚአብሔር <u>በንስሐና በቁርባን</u> ለመቅረብ - ”ዘመቻ ነፍስ” - የተቀደሰው ታላቁ የጌታ ጾም (ማቴዎስ ፬)።

ጽድቅን
የሚራቡና
የሚጠሙ
ብፁዓን ናቸው፥
ይጠግባሉና።

ማቴዎስ ፭፡፮

**የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ
እናንተ ደግሞ
በኑሮአችሁ ሁሉ
ቅዱሳን ሁኑ።**

፩ኛ ጴጥሮስ ፩፥፲፮

አያሌ ቀንም
አዝን ነበር
በሰማይም
አምላክ ፊት
እጾምና እጸልይ
ነበር።

ነህምያ ፩፡፬

## በዚህ ቀን ከሚታሰቡት መካከል

ሶርያዊያን አባቶች ቅዱስ በርሱማ (የሶርያውያን መነኮሳት አባት) እና ቅዱስ ጳውሎስ

### ለማወቅና ለማድረግ

ይህ ሳምንት ”ቅድስት” ይባላል- ይኸውም ”ዛቲ ዕለት ቅድስት ይእቲ” ከሚለው ዋዜማ መነሻ ቃል ወስዷል። የሰንበት ክርስቲያንን ከዕለታት ተለይታ ቅድስት መሆንዋን ያስታውሳል።

ዐቢይ ጾም የየራሳቸው መጠሪያና ምክንያት ባላቸው በ፰ ሳምንታት (ከእሁድ እስከ ቅዳሜ) ይከፈላል። እነዚህም ከዛሬ ጀምሮ ዘወረደ፤ ከዛ ቅድስት ፤ከዛ ምኩራብ ፤ከዛ መጻጉዕ ፤ከዛ ደብረ ዘይት፤ ከዛ ገብር ኄር ፤ከዛ ኒቆዲሞስ፤ ከዛ ሆሳዕና (ሰሙነ ሕማማት የሚጀምርበት)።